# الأذكار التي تقال صباحًا ومساءً

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

ጧትና ማታ የሚባሉ ዚክሮች

(اللَّهُ لا إِلَهَ إِلا هُوَ الْحَيُّ الْقَيُّومُ لا تَأْخُذُهُ سِنَةٌ وَلا نَوْمٌ لَهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الأَرْضِ مَنْ ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِنْدَهُ إِلا بِإِذْنِهِ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ وَلا يُحِيطُونَ بِشَيْءٍ مِنْ عِلْمِهِ إِلا بِمَا شَاءَ وَسِعَ كُرْسِيُّهُ السَّمَوَاتِ وَالأَرْضَ وَلا يَؤُودُهُ حِفْظُهُمَا وَهُوَ الْعَلِيُّ الْعَظِيمُ).

(አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ሕያው ራሱን ቻይ ነው፡፡ ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም፡፡ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፡፡ ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል፡፡ በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)፡፡ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ፡፡ ጥበቃቸውም አያቅተውም፡፡ እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው፡፡)

(አያቱል ኩርሲይ አል በቀራህ፡ 255)

(آمَنَ الرَّسُولُ بِمَا أُنْزِلَ إِلَيْهِ مِنْ رَبِّهِ وَالْمُؤْمِنُونَ ۚ كُلٌّ آمَنَ بِاللَّهِ وَمَلائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ لا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِنْ رُسُلِهِ وَقَالُوا سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ الْمَصِيرِ * لا يُكَلِّفُ اللَّهُ نَفْساً إِلا وُسْعَهَا لَهَا مَا كَسَبَتْ وَعَلَيْهَا مَا اكْتَسَبَتْ رَبَّنَا لا تُؤَاخِذْنَا إِنْ نَسِينَا أَوْ أَخْطَأْنَا رَبَّنَا وَلا تَحْمِلْ عَلَيْنَا إِصْراً كَمَا حَمَلْتَهُ عَلَى الَّذِينَ مِنْ قَبْلِنَا رَبَّنَا وَلا تُحَمِّلْنَا مَا لا طَاقَةَ لَنَا بِهِ وَاعْفُ عَنَّا وَاغْفِرْ لَنَا وَارْحَمْنَا أَنْتَ مَوْلانَا فَانْصُرْنَا عَلَى الْقَوْمِ الْكَافِرِينَ).

(መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ፡፡ ምእምኖቹም (እንደዚሁ)፡፡ ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣

በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል አንለይም» (የሚሉ ሲሆኑ) አመኑ። «ሰማን፤ ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም። *

አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም። ለርስዋ የሠራችው አላት። በርስዋም ላይ ያፈራችው (ኀጢአት) አለባት። (በሉ)፡- ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን፤ (አትቅጣን)። ጌታችን ሆይ! ከባድ ሸክምን ከእኛ በፊት በነበሩት ላይ እንደጫንከው በእኛ ላይ አትጫንብን። ጌታችን ሆይ! ለኛም በርሱ ችሎታ የሌለንን ነገር አታሸክመን። ከእኛም ይቅርታ አድርግ ለእኛም ምሕረት አድርግ። እዘንልንም፤ ዋቢያችን አንተ ነህና። በከሓዲዎች ሕዝቦች ላይም እርዳን።)

(አል በቀራህ 285 - 286)

(قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ) (قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ الْفَلَقِ) (قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ النَّاسِ).

(በል «እርሱ አላህ አንድ ነው።)

(በል «በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ።)

(በል «በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ።)

ሙሉ ምዕራፉን (አል'ኢኽላስን፣ አል'ፈለቅን እና አንናስን) ሦስት ጊዜ ይነበባሉ።

أعوذ بكلمات الله التامات من شر ما خلق.

«አዑዙ ቢከሊማቲላሂ አትታማቲ ሚን ሸሪ ማ ኸለቀ» (ምሉዕ በሆኑት የአላህ ቃላት ከፈጠራቸው ነገሮች ክፋት እጠበቃለሁ።) (ሦስት ጊዜ) ይባላል።

بسم الله الذي لا يضر مع اسمه شيء في الأرض ولا في السماء وهو السميع العليم.

«ቢስሚላሂ ለዚ ላ የዱሩ መዐ_ስሚሂ ሸይኡን ፊል አርዷ ወላ ፊ ስሰማኢ ወሁወ አስ'ሰሚዑል ዐሊም።» (በዚያ ከስሙ ጋር በምድርም ይሁን በሰማይ ምንም ነገር የማይጎዳ በሆነው እንዲሁም ሰሚና ዐዋቂ በሆነው አላህ ስም።) (ሦስት ጊዜ) ይባላል።

رضيت بالله ربًّا وبالإسلام دينًا وبمحمد صلى الله عليه وسلم نبيًّا.

«ረዷቱ ቢልላሂ ረበን ወቢል ኢስላሚ ዲነን ወቢ ሙሐመዲን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ነቢየን»
(የአላህን ጌትነት ፣ የእስልምናን ሃይማኖትነት፣ የሙሐመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ነብይነት ወደድኩ (ተቀበልኩ)።) (ሦስት ጊዜ) ይባላል።

أصبحنا وأصبح الملك لله والحمد لله لا إله إلا الله وحده لا شريك له، له الملك وله الحمد وهو على كل شيء قدير، رب أسألك خير ما في هذا اليوم وخير ما بعده، وأعوذ بك من شر ما في هذا اليوم ومن شر ما بعده، ربِّ أعوذ بك من الكسل والهرم وسوء الكِبَر، وأعوذ بك من عذاب النار وعذاب القبر.

«አስበሕና ወአስበሐል ሙልኩ ሊላሂ፤ ወልሐምዱ ሊላሂ፤ ላኢላሃ ኢለላሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ረብቢ አስአሉከ ኸይረ ማ ፊ ሀዘል የውሚ ወኸይረ ማ በዕደሁ፤ ወአዑዙ ቢከ

ሚን ሸርሪ ማ ፊ ሀዘል የውሚ ወሚን ሸሪ ማ በዕደሁ፤ ረብቢ አዑዙ ቢከ ሚነል ከሰሊ ወል ሀረሚ ወሱኢል ኪበር፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢ አንናሪ ወዐዛቢል ቀብር።» (እኛም አነጋን፤ ንግስናም የአላህ ሆኖ አነጋ። ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው። ከአላህ ውጭ (በእውነት) የሚመለክ አምላክ የለም ፤ ብቸኛና አጋር የሌለው ነው ፤ ንግስና እና ምስጋና ለርሱ ነው ፤ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው። ጌታዬ ሆይ! በዚህ ቀን ውስጥም ከዚህ ቀንም በኋላ ያለን መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ። በዚህ ቀን ውስጥም ከዚህ ቀንም በኋላ ካለው ክፉ ነገርም በአንተ እጠበቃለሁ። ጌታዬ ሆይ! ከስንፍና ፣ ከመጃጀትና ከመጥፎ እርጅና በአንተ እጠበቃለሁ። ጌታዬ ሆይ! ከእሳት ቅጣት እና ከቀብር ቅጣት በአንተ እጠበቃለሁ።) ምሽት ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

أمسينا وأمسى الملك لله،

እኛም ንግስናም የአላህ ሆነን አመሸን። ... እንዲህም ይላል፡-

رب أسألك خير ما في هذه الليلة...

(ጌታዬ ሆይ የዚህንም ሌሊት እና ከዚህ ሌሊት በኋላም ያለን መልካም ነገር እማፀንሀለሁ... እስከመጨረሻው አዝካር ድረስ፡ (እኛም ንግስናም የአላህ ሆኖ አነጋን።) እና (በዚህ ቀን ውስጥ) በሚለው ፈንታ።

اللهم بك أصبحنا وبك أمسينا وبك نحيا وبك نموت واليك النشور.

«አልላሁምመ ቢከ አስበሕና ወቢከ አምሰይና ወቢከ ነሕያ ወቢከ ነሙቱ ወኢለይከ_ንኑሹር።» (ጌታዬ ሆይ! በአንተ (ጥበቃ) አነጋን ፤ በአንተ (ጥበቃም) አመሸን ፤ በአንተ (ስም)

ህያው እንሆናለን ፤ በአንተ (ስምም) እንሞታለን ፤ መቀስቀስም ወደ አንተ ብቻ ነው።) ምሽት ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

اللهم بك أمسينا وبك أصبحنا وبك نموت وبك نحيا وإليك المصير.

«አልላሁምመ ቢከ አምሰይና ወቢከ አስበሕና ወቢከ ነሙቱ ወቢከ ነሕያ ወኢለይከል መሲር።» (ጌታዬ ሆይ! በአንተ (ጥበቃ) አመሸን በአንተ (ጥበቃም) አነጋን ፤ በአንተ (ስም) ህያው እንሆናለን በአንተ (ስም) እንሞታለን። መመለሻም ወደ አንተ ብቻ ነው።)

اللهم ما أصبح بي من نعمة أو بأحد من خلقك فمنك وحدك لا شريك لك فلك الحمد ولك الشكر.

«አልላሁምመ ማ አስበሐ ቢ ሚን ኒዕመቲን አው ቢአሐዲን ሚን ኸልቂከ ፈሚንከ ወሕደከ ላ ሸሪከ ለከ ፈለከል ሐምዱ ወለከ አሽሹክሩ።» (አላህ ሆይ! በኔ ወይም ከፍጡራንህ በአንዱ ላይ ያነጋው ፀጋ ከአንተው ብቻና ብቻ ነው። ለአንተ አጋር የለህም ምስጋናና ውዳሴም ይገባሀል። ምሽት ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

ما أمسى بي.

(በኔ ላይ ያነጋው በሚለው ፈንታ) በኔ ላይ ያመሸው።

(ሦስት ጊዜ።)

اللهم إني أسألك العافية في الدنيا والآخرة، اللهم إني أسألك العفو والعافية في ديني ودنياي وأهلي ومالي، اللهم استر عوراتي وآمن روعاتي، اللهم احفظني مِن بين يديَّ ومِن خلفي وعن يميني وعن شمالي ومن فوقي، وأعوذ بعظمتك أن أُغتال من تحتي.

«አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ዓፊየተ ፊድዱኒያ ወል አኺረቲ፤ አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ዐፍወ ወል ዓፊየተ ፊ ዲኒ ወዱንያየ ወአህሊ ወማሊ፤ አልላሁምመ ስቱር ዐውራቲ ወአሚን ረውዓቲ፤ አልላሁምመ ኢሕፈዝኒ ሚን በይኒ የደይየ ወሚን ኸልፊ ወዐን የሚኒ ወዐን ሺማሊ ወሚን ፈውቂ፤ ወአዑዙ ቢዐዞመቲከ አን ኡግታለ ሚን ተሕቲ።» (አላህ ሆይ! በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ጤናን እጠይቅሀለሁ። አላህ ሆይ! በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም በሃይማኖቴ እና በቅርቢቱ ዓለም ህይወቴ በቤተሰቦቼም በንብረቴም ይቅርታህንና ጤናን እጠይቅሃለሁ። አላህ ሆይ! ነውሬን ሸፍንልኝ። ለስጋቴ (ለፍርሃቴ) ደህንነትን ለግሰኝ። አላህ ሆይ! ከፊት ለፊቴ ከኋላዬም ከበስተቀኜም ከበሰተግራዬም ከበላዬም ጠብቀኝ። ከበታቼም እንዳልጠቃ በልቅናህ እጠበቃለሁ።)

اللهم أنت ربي لا إله إلا أنت، خلقتني وأنا عبدك وأنا على عهدك ووعدك ما استطعت، أعوذ بك من شر ما صنعت، أبوء لك بنعمتك عليّ، وأبوء بذنبي، فاغفر لي فإنه لا يغفر الذنوب إلا أنت.

«አልላሁምመ አንተ ረቢ ላኢላሀ ኢልላ አንተ ኸለቅተኒ ወአነ ዐብዱከ ወአነ ዐላ ዐህዲከ ወወዕዲከ መስተጠዕቱ፤ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማሰነዕቱ፤ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዓለይየ፤ ወአቡኡ ቢዘንቢ፤ ፈግፊር ሊ ፈኢነሁ ላ የግፊሩ አዝ-ዙኑበ ኢልላ አንተ።» (አላህ ሆይ! አንተ ጌታዬ ነህ። ከአንተ በስተቀር ሌላ በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ፈጥረኸኛል። እኔም ባርያህ ነኝ። ላንተ የገባሁትን ቃል ኪዳን ለመሙላት የቻልኩትን ያህል እጥራለሁ። (የገባህልኝንም) ቀጥሮ

አምናለሁ። ከሰራሁት ነገር ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ።በኔ ላይ ለዋልከው ፀጋም እውቅናን እሰጣለሁ። ኃጢአት መስራቴንም አምናለሁ። ምህረትህን ለግሰኝ። እነሆ ካንተ በስተቀር ኃጢአትን የሚምር ማንም የለምና።)

اللهم فاطر السماوات والأرض، عالم الغيب والشهادة، ربَّ كل شيء ومَلِيكه، أشهد أن لا إله إلا أنت، أعوذ بك من شر نفسي ومن شر الشيطان وشركه وأن أقترف على نفسي سوءاً أو أجُرَّه إلى مسلم.

«አልላሁምመ ፋጢረስ_ ሰማዋቲ ወል አርዲ፤ ዐሊመል ገይቢ ወሽ_ሸሃደቲ፤ ረብበ ኩሊ ሸይኢን ወመሊከሁ፤ አሽሀዱ አን ላኢላሀ ኢልላ አንተ፤ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ነፍሲ ወሚን ሸርሪሽ_ሸይጧኒ ወሺርኪሂ ወአን አቅተሪፈ ዐላ ነፍሲ ሱአን አው አጁረሁ ኢላ ሙስሊም።» (የሰማያትና የምድሩ ፈጣሪ የሆንከው፣ የሩቁን እና የቅርቡን አዋቂ ፤ የሁሉም ነገር ጌታ እና ባለቤት የሆንከው አላህ ሆይ! ከአንተ በስተቀር ሌላ በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ። ከነፍሴ ተንኮል እንዲሁም ከሸይጧን ተንኮል እና የሽርክ ጥሪው (ውትወታው)፣ በነፍሴ ላይ መጥፎ ከመስራትም ይሁን ሙስሊም በሆነ ሰው ላይ መጥፎን ከመፈፀም በአንተ እጠበቃለሁ።)

اللهم إني أصبحت أُشهدُك وأشهد حملة عرشك وملائكتك وأنبياءك وجميع خلقك بأنك أنت الله لا إله إلا أنت وأن محمداً عبدك ورسولك.

«አልላሁምመ ኢንኒ አስበሕቱ ኡሽሂዱከ ወኡሽሂዱ ሐመለተ ዐርሺከ ወመላኢከቲከ ወአንቢያአከ ወጀሚዐ ኸልቂከ ቢአንነከ አንተ አልላሁ ላ ኢላሀ ኢልላ አንተ ወአንነ ሙሐመደን ዐብዱከ ወረሱሉከ» (አላህ ሆይ! አንተ አምላክ

መሆንህን ከአንተ በስተቀርም በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን እና ሙሐመድም ባርያህና መልዕክተኛህ መሆናቸውን አንተን፣ የዐርሽህን ተሸካሚዎች፣ መላእክትህን፣ አንቢያኦችህን (ነብያቶችህን) እንዲሁም ሁሉንም ፍጡራኖችህን ምስክር አድርጌ አነጋሁ።) በምሽት ደግሞ

اللهم إني أمسيت...

«አሏሁመ ኢኒ አምሰይቱ» ( ... አስመስክሬ አመሸሁ።) እስከመጨረሻው (አራት ጊዜ)።

«ላኢላሀ ኢለላሁ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር።» (ከአላህ ውጭ በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ተጋሪም የለውም። ንግስናም ምስጋናም የሚገባው ለእርሱ ብቻ ነው። እርሱ በነገሮች ላይ ሁሉ ቻይ ነው።) (መቶ ጊዜ) ንጋት ወይም ምሽት ላይ።

حسبي الله لا إله إلا هو عليه توكلت وهو رب العرش العظيم.

«ሐስቢየልላሁ ላ ኢላሀ ኢላ ሁው፤ ዐለይሂ ተወከልቱ፤ ወሁወ ረቡል ዐርሺል ዐዚም።» (አላህ በቂዬ ነው፤ ከእርሱ በቀር ሌላ በእውነት የሚመለክ የለም፤ በእርሱ ተመካሁ፤ እርሱም የታላቁ ዐርሽ ጌታ ነው።) (ሰባት ጊዜ)

سبحان الله وبحمده

«ሱብሓነ'ላሂ ወቢሐምዲሂ።» (ጥራት እና ምስጋና ለአላህ ተገባው።) (መቶ ጊዜ) ሲነጋ እና ሲመሽ። ወይም በሁለቱም ወቅት።

أستغفر الله وأتوب إليه.

«አስተግፊሩላሀ ወአቱቡ ኢለይሂ» (አላህን ምህረቱን እጠይቀዋለሁ፤ ወደ እርሱም በፀፀት እመለሳለሁ።) (መቶ ጊዜ።)

ለመጻፍ የገራልኝ ይህን ያክል ነው፤ ሌሎች የሚጠቀሙበት እንዲያደርገው አላህን እማጸነዋለሁ።

ጸሐፊ ሙሐመድ አስ'ሷሊሕ አል'ዑሠይሚን (አላህ ይዘንላቸው) ቀን 20-1-1418 ሂ

# ማውጫ

No table of contents entries found

am312v2.0 - 04/09/2026